# የሰሜን አሜሪካ የኢሕአፓ አባላት መደበኛ ጉባኤውን አጠናቀቀ

በካናዳ ዋና ከተማ ኦታዋ ውስጥ ከግንቦት 21 እስከ ግንቦት 23 1996 ዓ/ም ለሦስት
ተከታታይ ቀናት መደበኛ ጉባዔውን ሲያካሂድ የሰነበተው የሰሜን አሜሪካ የኢሕአፓ ክፍል
አገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ ያለችበትን ሁኔታ በመመርመር በተለያዩ ድርጅታዊ ጉዳዮ
ች ላይ ሰፊ ውይይት አካሂዶ ትግሉን የሚያጠናክሩ ተገቢ መመሪያዎችን በማስተላለፍ ጉባ
ዔውን አጠናቋል፡፡

ጉባዔው፥ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት በሚወስዳቸው አፍራሽ ፖሊሲዎች ምክንያት፥
የአገሪቱ ችግሮች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሱ መሄዳቸውና ሕዝቡም በአስከፊና ባሳዛኝ የኑሮ
ሁኔታ ላይ የሚገኝ መሆኑን ተገንዝቧል፡፡ የፖለቲካ ሥልጣን በሞኖፖሊ መያዙን፥ ዜጎች በ
ፖለቲካ አመለካከታቸው ብቻ የሚገደሉ፥ የሚሰደዱ፥ የሚታሠሩና መዳረሻቸው የሚጠፋ
መሆኑን፥ የሀገሪቷም ሀብት በተለየያዩ ዘዴዎች በገዥው ክፍል ባለሥልጣኖች የሚበዘበዙና
የሚዘረፉ መሆኑን ጉባኤው አጢኗል፡፡

ወያኔ በሚያራምደው የዘረኝነት ፖሊሲ ምክንያት፥ በአሁኑ ግዜ እየደረሰ ያለው አስ
ከፊ የዜጎች እልቂት አሳሳቢ ደረጃ ላይ በመድረሱ፥ በተለይም በያዝነው ዓመት በአኝዋኮች ላ
ይ የተፈፀመውን የዘር ማጥፋት ዘመቻና በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች እየደረሰ ያለውን እል
ቂት በፅኑ ኮንኖ ይህንን አረመኔያዊ ተግባር የፈፀሙ የሥርዓቱ ሎሌዎች በአስቸኳይ ለፍርድ
እንዲቀርቡ ጠይቋል፡፡

በአዲስ አበባ፥ በናዝሬት፥ በጅማ ፥ በአምቦ፥ በዲላ --ወዘተ የመብት ጥያቄ ባነሱ የ
ዩኒበርስቲና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ የሚያደርሰውን አፈና ፥ ጭፍጨፋና ከትምህር
ት ገበታ የማባረር ተግባር ከገዢው ቡድን አደንቁሮ የመግዛት ፍላጎት የመነጨ ኋላ ቀር አ
መለካከት መሆኑን በመገንዘብ ባስቸኳይ እንዲቆምና ተማሪዎችም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ
ወደ ትምሕርት ገበታቸው እንዲመለሱ እያሳሰበ፥ የትምሕርት ተቋማትም የእውቀት መገብ
ያእንጂ የካድሬዎች መፈንጫ መሆናቸው ቀርቶ ለወደፊቱ ሀገሪቱን ለመምራት ብቃት ያላ
ቸውን ዜጎች ማፍሪያ እንዲሆን የመብት ጥያቄውን ትግል በሕብረት እንዲገፉበትና ሕብረተ
ሰቡም ከጎናቸው እንዲቆም ጥሪውን አስተላልፏል፡፡

በመንግሥት ቸልተኝነት የተነሳ በአስደንጋጭ ፍጥነት እየተስፋፋና ሕዝባችንን እየፈ
ጀ ያለው የኤድስ በሽታ የደረሰበት ደረጃ ከቁጥጥር ውጪ ከመሆኑ በፊት ስለ በሽታው የሚ
ያብራሩ የመከላከያ ትምሕርቶችና በበሽታው ለተጠቁ ወገኖቻችን የእድሜ ማራዘሚያ መድ
ሃኒቶችን በበቂ ለማዳረስ የሚያስችል ስፋትና ጥልቀት ያለው ብሔራዊ ፓሊሲ መኖሩ የግድ
አስፈላጊ መሆኑን ተገንዝቧል፡፡

ሥልጣን ላይ ያለው ቡድንም የሀገሪቱን ሀብት በፈለገው መንገድ ከማባከን፥ የጠባብ
ናየግል ፍላጎቱን ለማርካት ከመሯሯጥ ታቅቦ የዚህን ብሄራዊ ችግር ክብደት በመገንዘብ ለበ
ሽታው ከክብደቱ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የበጀትና የባለሞያ ድጋፍ እንዲያደርግ እያሳሰበ፥ ሕ
ዝቡም ለዚህ ፖሊሲ ተግባራዊነት የገዢውን ቡድን በማስጨነቅና በማስገደድ መብቱን እን
ዲጠቀም ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

ሕዝብን ከቦታ ወደ ቦታ በማስፈር ስም የውጭ መንግሥታትንና የግብረ ሰናይ ድር
ጅቶችን ገንዘብ ለማግኘት ሲባል ብቻ በጥናት ላይ ያልተመረኮዘ የግብር ይውጣ የሰፈራ ሥ

ራንግከናወን በተፈናቃዮቹና በሚሰፍሩበት አካባቢ ያለውን ሕዝብ ሕይወት ከማመሰቃቀሉም በስተቀር የፈየደው ቁምነገር አለመኖሩን ጉባኤው ተገንዝቧል።

የወያኔን ካዝና ለመሙላትና በሰፈራ ስም ለዓመታት ሲመኘውና በትጋት ሲሰራው የነበረውን የሕዝቦች መጋጨትና መናቆርን በቀላሉ ለማስፈፀም እየዋለ ያለ ተግባር ከፍተኛ ጉዳት ከማድረሱ በፊት እንዲቆም እየጠየቀ ጉዳዩ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ በቂ ጥናት ተደርጎበት የሕዝቡም ፍላጎት ተጠይቆ ሊሰራ እንደሚችል አጢኖታል።

በአሁኑ ጊዜ በሃገር ውስጥና በውጪ የሚገኘውን ሕብረተሰብ በአንድ ላይ አስተባብሮ በሕዝባችን ላይ እየደረሰ ያለውን ችግር ለማስወገድና የሀገራችንን ገፅታ ለመለወጥ ከፍተኛ የሆነ ሰላማዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች ሕብረትን በሙሉ ልብ እንደሚደግፍና የትግሉም አጋር በመሆን ከጎኑ እንደሚሰለፍ አረጋግጧል።

በተጨማሪም ሕብረቱ የሚያደርገው ሰላማዊ ትግል ጠቀሜታው የሕዝባችንና የተቃዋሚው ክፍል ብቻ ሳይሆን በስልጣን ላይ ያለውም አምባገነናዊ ቡድን ሊደርስበት ከሚችለው የከፋ አደጋ እንዲድንና የዲሞክራሲያዊ ስርዓቱ ግንባታ ተካፋይና ተጠቃሚ እንዲሆን ሊያደርገው እንደሚችል በመገንዘብ የቀረበለትን የሰላማዊ ትግል ጥሪ ቅድመ ሁኔታዎች ያለ ምንም ሰበብ ተቀብሎ ለተግባራዊነታቸው በጎ ምላሽ እንዲሰጥ አሰገንዝቧል።

በሀገር ውስጥና በውጭ የሚገኙ የሙያ፥ ሲቢክና የሰብአዊ ድርጅቶች ለትግሉ የሚያደርጉትን አስተዋፅኦ አድንቆ አጋርነታቸው በከፍተኛ ደረጃ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪውን አስተላልፏል።

ኢትዮጵያ በቆራጥ ልጆቿ የተባበረ ትግል አንድነቷን ጠብቃ ትኖራለች
የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ )

ግንቦት 1996